# <u>ኪነጥበብ የህዝብ ንብረት እንጂ! የፖለቲካ ካድሬዎች ማላገጫ አይደለችም!</u>

ዘነበ በቀለ

ኪነ ጥበብ ተፈጥሮን፣ ፍጥረትን በጠለቀ ስሜት የምትመለከትበት፣ ልማትን ጥፋትን አጉልታ የምታይበት የጠራ መነፅር ያላት ህዝባዊ መሳሪያ ናት። በማህበረሰቡ ውስጥ የምትመለከተውን በጎ ነገር ለማወደስ ቅንነቱ፤ መጥፎውንም ነቅሶ በማውጣት ለመኮነን ድፍረቱ ያላት ናት። አንዳችም ምድራዊ ሀይል ሊገድበው የማይችል ህዝባዊ እምነትና ፅናት ያላቸው ጥበበኞችን የምታፈራ እንጂ! ሀቀኛ የሆነ ትርጉሟን አዛብታ በህዝብ ጠላቶች ጎራ ተሸሞንሙና የምትኖር አይደለችም ኪነጥበብ። ስለዚህም ነው በአማኞቿ ብርታትና ፅናት የተከበረና የተወደደ ለመሆን የበቃችው። ይህን ሀቅ ስተው በግል ጥቅማጥቅም ከዘመን ድንበር ተሻግረው የማይመለከቱ ጊዜያውያን እጅ! ከወደቀች በእርግጥም ኪነ ጥበብ የውርደት ማቅ ለበሰች እንጂ! አደገች ተመነደገች ማለት አይቻልም።

በሀገራችን የሙዚቃና የድራማ ስራ ውስጥ በወዶ ገብነት የተቀላቀሉ የሙያው አፍቃሪዎች የሙያውን ስነምግባር ማክበር ግዴታ ይሆናል። በጊዜያዊው የገበያ ግርግር ተታለው የኪነትን ሀቀኛ ገፅታ ለመበረዝ ከሚያስችል ድርጊት ውስጥ ራሳቸውን ማስገባት አይኖርባቸውም። በህዝብ ባህላዊ ንብረት ላይ ተመርኩዞ፣ የህዝብን ስነ ልቡናዊ ግንዛቤ ለመሸርሸር የሚደረግ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ በኪነጥበብ ላይ የሚደረግ ደባ ከመሆን አያልፍም። ስለዚህም በሙያው ውስጥ የተሰለፉ ሁሉ በቅድሚያ ሊረዱት የሚገባው ሙያውን አክብሮና አስከብሮ ሌላውን ጠቅሞ ራስንም ተጠቃሚ ለማድረግ ህዝባዊውን ባህል ለመሰረዝም ሆነ ለመበረዝ የማያስችል ብቃት እንዲኖር ራስን በዚህ በኩል ማዘጋጀት የግድ ይላል።

ሙዚቃ በዓለም ውስጥ በህዝብ ዘንድ አጠቃላይ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚያስችል በመሆኑ አለምአቀፋዊ ቋንቋ ነው የሚል ቅፅል የተሰጠው ነው። አለም አቀፋዊ የሚለው አባባል የሚመነጨው በሚከተለው የድምፅ ገደብና ስኬል ተመርኩዞ ነው። በብዙ መልኩ ቢታይ የሰው ልጅ ሊሰማው በሚችለው ድምፅ ላይ ነው ግምጋሜውን የሚያውለው። እነዚህ የሚሰማቸው የድምፅ አይነቶች ደግሞ በተደጋጋሚነት ሲደመጡ ቀራቢ የሆኑ ወዲያው ሊታወቁ የሚችሉ ድምፆች ይሆናሉ። በነዚህ ድምፆች ላይ በመመስረት የዜማ መሰላሎችን ወይም ስኬሎችን መፍጠር ይቻላል ማለት ነው። በመሆኑም ነው በርካታ የባህል ሙዚቃዎች በየአካባቢያቸው ነዋሪ ህዝብ ዘንድ በቅርብ ሊስተዋሉና ሊደመጡ የሚቻልበት ደረጃ ላይ የደረሱት። በሩቅ ምስራቅና፤ በአፍሪቃ በተለይም በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በሱዳን፣ ሙዚቃዎች ላይ የሚስተዋለው የፔንታቶኒክ ወይም የአምስት ድምፅ መሰላል በነዚህ አህጉራት የሚኖረውን ህዝብ ሁሉ የሙዚቃ ስሜቱን ሊኮረኩር የሚችል ነው። ያ! ማለት ግን አውሮጳውያን የሚጠቀሙበትን የዲያቶኒክ ድምፅ መሰላል የሚከተለውን የሙዚቃ አይነትና ስልት ይጠሉታል ወይም ሊገባቸው አይችልም ማለት አይደለም።

የሙዚቃ ግንዛቤ በተለያየ መልኩ የሚንፀባረቅ ሲሆን፣ አንደኛው በባህል ሙዚቃ ላይ እና በቋንቋ ላይ መሰረት ያደረገ ነው። ሁለተኛው በሙዚቃው አይነትና የመሳሪያ ቅንብር ወይም በዜማው ውበት በተለይም ሜላንኮሊክ አቀራረብ ላይ ተመርኩዞ የሚደረግ ስሜትን የመኮርኮር ግንዛቤ ነው። ሶስተኛው ደግሞ የአድማጩን የዜማ ብስለት የሚለካ ወይም የሙዚቃ ትምህርቱን የሚያመላክት ያለምንም ቃላት ዕርዳታ የዜማ ባህርይን በድምጫ ብቻ የሚለይ፣ አንድን ሙዚቃዊ ታሪክ ተገንዝቦ

የመፍታት አቅም ያለው የአድማጭ ክፍል ነው። ይህ ሁኔታ በተነፃፃሪነት ቢታይ መጀመሪያ ፊደል፣ ከዚያ ወንጌል፣ ከዚያም ዳዊትን ጨርሶ፣ ማንበብና መፃፍ እንደሚቻል ያላወቀ ተማሪ፣ ፊደልን ተምሮ የወንጌልንም ሆነ የዳዊትን ምስጢር ሳይመረምር፣ ግጥም ልግጠም ብሎ እንደሚነሳ ያስቆጥረዋል። ይህ አይነቱ አነሳስ ደግሞ ከልማቱ ጥፋቱ ያመዝናል። ማንኛውም ነገር የራሱ የሆነ የዕድገት እርምጃ አለው። ዕድገቱን ጠብቆ ሲጓዝ ብቻ ነው ጠቃሚነቱ ጎልቶ የሚታየው። የኢትዮጵያን ሙዚቃ አስመልክቶ ደረጃው ከባህል ሙዚቃ አልፎ አልሄደም። በተለያዩ መልኮች የሚንፀባረቁት የህዝብን ስሜት ለመኮርኮር በሚደረጉ ስራዎች ላይ መሆኑ ይህን ሀቅ ተመርኩዞ ነው።

በእርግጥ ለሰላም ለሀገር ብልፅግና ለወገን በጎነት የሚጠቅሙ ነገሮችን ህዝብ ሊገባው በሚችል ቋንቋ ቢነገረው፤ አንድነትን ፍቅርን ቢሰበክ ይህ ከሙያው ኤቲክስ ያፈነገጠ አሰራር ነው ሊባል አይገባው ይሆናል በተለይም ከላይ እንደተገለፀው የጥበቡ ዕድገት ደረጃ በተገደበበት ማህበረሰብ መሃል። ነገር ግን የሙዚቃን የመወደድ ሀይል ተንተርሶ በህዝብ ላይ የሚደረግ ስነ ልቡናዊ ተፅዕኖ፣ የጥበቡን ታማኝነት ያረክሳል። በከፍተኛ ደረጃ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚገባው፤ የህዝብ ስሜት በራሱ በህዝቡ የሚገለፅ እንጂ በሶስተኛ ክፍል አራጋቢነት የሚፈጠር አይደለም። በታሪክ እንደሚታየው የቀረርቶንና የፉከራን ዜማ ያዜም የነበረው ዘማቹ ህዝብ እንጂ! ባለሙያተኛው አዝማሪ አልነበረም። ይህ ባለሙያ አብሮ ቢሰለፍ የድርሻውን ለማዋጣት እንደ አንድ ዘማች ሆኖ እንጂ! ሌላውን ለማደፋፈር ወይም ለማነቃቃት ብሎ አይደለም። እንዲያ እንኳ ቢያስብ በጦርነት ላይ ሁሉንም ሊደርስ የሚችልበት መድረክ አያገኝምና ሊሳካ አይችልም።

ለህዝቡ ለራሱ የሚተዉ ዜማዎችና ወቅቶች አሉ። እነዚህን ዜማዎች ማገለባበጥ የህዝቡ ወዳጅና ባለውለታ አያደርግም። የህዝቡን የማለት መብት ማስመስከሪያ የሆነውን ዜማውን ቀምቶ በአፈ ጉባኤነት ለማስተላለፍ መሞከር የህዝብ ተቆርቋሪ የሙያው አክባሪ አያሰኝም። እንደዚያውም ሁሉ በቀላልና በቅርብ ህዝብን ማታለል ይቻላል ብሎ አምኖ፣ ከልብ የሌለ ተቆርቋሪነትን የቋንቋ አቀንቃኝ ሆኖ የሙዚቃን አለምአቀፋዊነት ስቶ መጓዝ የጥበቡ አስፋፊነትን ተግባር አይመሰክርም። እናም! የኢትዮጵያ የጥበብ ሰዎች ትኩረታቸውን በሙያው ላይ እንጂ በሚያስገኘው ጥቅም ላይ አድርገው ከተንቀሳቀሱ ይዋል ይደር እንጂ! ከህዝቡ ጋር አይንና ናጫ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለውም። በታሪክም የመጠየቅ ዕድል እንዳይገጥማቸው ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታቸው ነው። ማንም እነተኛ የጥበቡ ወዳጅ በመጀመሪያ ፍቅሩን የሚያሳየው ለጥበቡ እንጂ ጥበቡ ለሚያስገኘው ጥቅም እንዳይሆን መጠንቀቅ አለበት። ያ! ከሆነ ግን ግዜያዊውን ግርግር መከታ አድርጎ ወደ ጥበቡ ጎራ የተቀላቀለ እንጂ የሙያው አፍቃሪ እንዳልሆነ በጥብቅ ሊገነዘበው ይገባል። በየትኛውም መለኪያ ቢሆን በህዝብና፣ ህዝብ ባፈራው የኢትዮጵያዊነት ባህል ላይ፣ በሀገር ድንበርና በህዝብ ልዑላዊነት ላይ የተነሳን የወንበዴ መንጋ አረመኔያዊ ተግባር በዳንስና በጭፈራ አጅቦ ህዝብን ለማዋዛት እንደደላው አድርጎ ለማሳየት መጣር፤ የግል ምኞትንና ጥቅምን ለማስከበር ከሚደረግ ጥረት ውጭ ሌላ ህዝባዊ የሆነ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም።

በዚህ አይነቱ ቅሌት ውስጥ እጃቸውን ያስገቡ አዛውንትም ሆኑ ወጣት የሙያው ሰዎች በአስቸኳይ እጃቸውን እንዲያወጡ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ በማንም የግል አሳቢዎች ፍላጎትና ምኞት የተፈጠረች አገር አይደለችም። ወደፊትም ቢሆን በዚህ አይነቶቹ ሰዎች ልትጠፋ የማትችል ሀገር እንደሆነች መታወቅ አለበት።

የኢትዮጵያ ወጣቶች "ትግሉ ነው ህይወቴ" ብለው በትግላቸው ጠንክረው ሲሰዉ ኢትዮጵያንና ህዝቧን በዕኩልነት በማየት እንጂ! በጠባብነት ዘቅጠው በመገኘት አይደለም። ህዝባዊ መዝሙራቸው አሁንም ቢሆን በሀቀኛ ልጆቿ ድምፅ ሲንቆረቆር የሚደመጠው፣ ባህልን ለልዩነት ቋንቋን ለመበዝበዣ መሳሪያነት፤ ሙዚቃን ለጠባብ ግብ ዓላማ ለማዋል ለሚፈልግ ሁሉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው። ኢትዮጵያ በዘፈን ተፈጥራ በዳንስ የምታበቃ ሀገር አይደለችም። የወያኔ ትምክህትና የተወጠረበት ፊኛ ይተነፍሳል። በዚህ ዙሪያ ለጥቅማጥቅም የተሰለፋችሁ የሙያው ሰዎች ወደ ህሊናችሁ ተመልሳችሁ ከህዝብ ጎን እንጂ! የአምባገንን አገዛዝን በመደገፍ፣ በዜማ ውበት፣ በግጥም ድሪቶ ለማሽሞንሞን የሚደረግ ጥረት ካለ ይቁም!! ኪነጥበብ የህዝብ አጋር እንጂ! የህዝብ ጠላት አይደለችም። የሀገር ባህል ነፀብራቅ እንጂ! የአምባገነን መሸሸጊያ ጎሬ አይደለችም። ከህዝብ ጎን በመቆም፣ ኪነጥበብን እናስከብራት!!

---